# ይህች ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም

## ትዕይንት አንድ

1. ከነ አቶ ዘሪሁን መኖሪያ ቤት

1.1 ከቤቱ በረንዳ ላይ

(አቶ ዘሪሁን የእረፍት ቀን ልብሳቸውን እንደ ለበሱ ተቀምጠው መጽሐፍ ያነባሉ)

1.2 ከግቢው ውስጥ ከቤቱ በጓሮ በኩል ካለ የልብስ ማጠቢያ ቦታ

1.2.1 የቤት ሠራተኛዋ ውቤ ከልብስ ማጠቢያው ላይ ልብስ እያጠበች የቤቱ ....... ወ/ሮ ሮዛ ከልብስ ማጠቢያው አካባቢው ካለው ከማዕደ ቤቱ በር ላይ ተቀምጣ በከሰል ምድጃ ላይ በተጣደ የሸክላ ድስት ወጥ ስትሰራ እንዲሁም በእድሜ በአሥራ ስድስት አካባቢ ያለችው ወጣት እሌኒ ከቤቱ የጓሮ በር አካባቢ ተቀምጣ የታጠቡ የመመገቢያ እቃዎችን በጨርቅ እየወለወለች ትደረድራለች። ሦስቱም ያሉት በሚተያዩበት ቦታ ላይ ነው።

ውቤ - በመጀመሪያ ልታጥበው የነበረውን ልብስ ከማጠቢያው ውስጥ አውጥታ ከጨመቀችው በኋላ ወደ ሁለተኛውና ከመጀመሪያው በንጹህ ውሃ ከተሞላው ማጠቢያ ውስጥ ትጨምርና ሊታጠቡ ከተዘጋጁት ልብሶች መሃል አንድ የወጣቶች የሚመስለውን ሱሪ መዛ ታወጣና ከማጠቧ በፊት ኪሶቹን መበርበር ትጀምራለች። ከሁለተኛው ኪስ ውስጥ የቀኝ እጇን ከታ አንድ የሲጋራ መለኮሻ ጨብጣ ታወጣና ጭብጧን ፈልቅቃ ከመዳፏ ላይ ያለውን የሲጋራ መለኮሻ ስትመለከት ደንገጥ ብላ እያሰበች ወደ ወ/ሮ ሮዛ መለስ ብላ ስታይ ዓይን ለዓይን ስለ ተጋጩ ደንግጣ  እየተርበተበተችና እየዞረች በእጆቿ የያዘችውን የሲጋራ መለኮሻውንና ሱሪውን  ከልብስ ማጠቢያው ውስጥ ትከትና ለማጠብ ታጎነብሳለች።

ወ/ሮ ሮዛ - ባጋጣሚ ወደ ውቤ እያዩ ሲከታተሏት ቆይተው ግራ በመጋባት - አ.ህ ... ውቤ!

ውቤ ደንገጥ ብላ ካጎነበሰችበት እየቀናችና እየዞረች - አ.ቤ.ት እትዬ --አቤት

ሮዛ - ም.ን -- ምን ነበር? የያዝሽው?

ውቤ - ኧ.ረ ኧ.ረ ምንም እትዬ

ሮዛ - ቆጣ ብለው ውቤ! አሁን ከሮቤል የሱሪ ኪስ ውስጥ የሆነ ነገር ስታወጪ አይቼሻለሁ....

አምጭልኝ ወደ እዚህ! ፍጥነት!

(መሸጋገሪያ ሙዚቃ ይገባል)

ውቤ - በተሰቀቀ ስሜት ወደ ማጠቢያው ዞራ አስቀድማ የጣለችውን የሲጋራ መለኮሻ ፈልጋ

ታወጣና ወደ ሮዛ ይዛ ትሄዳለች::

እሌኒ - ከተቀመጠችበት ቦታ እንዳለች የምትሰራውን ሥራ አቋርጣ በደነገጠ መንጓጓት

ታያቸዋለች::

ሮዛ - የሲጋራ መለኮሻው የውቤ ተብላለችና እያሰበች ኢ.ሃ የሲጋራ ማ.ቀ.ጣ.ጠ.ያ

ውቤ - ኧረ እትዬ ለሌላ ለሌለ ነገር ቢይዘው እንጂ

ሮዛ - ከተቀመጠችበት እየተነሳች - ዝም - ዝም በይ አንቺ

ወደ ቤቱ ፊት ለፊት የሚወስደውን

(ሙዚቃ ይገባል/

እሌኒን አለፈዋት መንገድ ይዘው መሄድ ይጀምራሉ::

እሌኒ - እናቷ የሲጋራ መለኮሻውን እያገላበጡና እያዩ ሲናገሩ እንደ ሰማች ክፉኛ ደንግጣ

አፏን በመዳፏ እየሸፈነች ወ.ይ.ኔ ጉድ ! ትልና እናቷ ከተቀመጡበት ተነስተው

አልፈዋት እንደ ሄዱ ከተቀመጠችበት ተነስታ በጓሮው በር እየተጣደፈች ገብታ

ትሰወራለች::

# ትዕይንት ሁለት

2. ከዚያው ቤት ከሳሎኑ ውስጥ

2.1 በጅምሩ ከሳሎኑ ውስጥ ካለው እና ከተከፈተው የቴሌቪዥን እስክሪን ውስጥ የድርጊት ፊልም (አክሽን) በቅርበት መታየት ጀምሮ ከቅርበት እየራቀ መታየቱን ይቀጥላል።

ሮቤል - ከቴሌቪዥኑ ፊት ለፊት ካለው ትልቅ ሶፋ ላይ በጀርባው ተኝቶ ፊልሙን በተመስጦ ሲመለከት ይታያል። ከደረቱ ላይ የተገለጠ የመማሪያ መጽሐፍ ይታያል። የሳሎኑ የጓዳ በር ተበርግዶ እየተከፈተ እሌኒ እየተጣደፈች ትገባለች።

ሮቤል - በበሩ መከፈት ደንግጦ ከተኛበት እየተደናበረና እየተነሳ በቀኝ እጁ ይዞት በነበረው የቴሌቪዥኑ መቆጣጠሪያ ቴሌቪዥኑን እያጠፋ ወደ እሌኒ ዞሮ ያያል። ደንግጦ በተነሳበት ጊዜ መጽሐፉ ከወለሉ ላይ ይወድቃል።

እሌኒ - በተከፈተው በር እየተጣደፈች ከገባች በኋላ ወደ ሮቤል ትራመድና ወዲያው ተመልሳ የገባችበትን በር ለመዝጋት ዞራ ትመለስና ትዘጋዋለች።

# ትዕይንት ሦስት

/ ከዚያው ቤት ከበረንዳው ላይ /

አቶ ዘሪሁን - አስቀድመው ተቀምጠውበት ከነበረው ወንበር ላይ እንደ ተቀመጡ ያነቡት የነበረውን መጽሐፍ እንዳጠፉት በግራ እጃቸው እንደ ያዙት በቀኝ እጃቸው ከላይ ባለቤታቸው ሮዛ ከውቤ የተቀበሉትን የሲጋራ መለኮሻ ይዘውት በጣቶቻቸው እያፍተለተሉትና እያዩት አንገታቸውን እየነቀነቁ እ.ህ. “ይህች ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም” የሚባለው ተረት -- ይሄው አደራ!

ወ/ሮ ሮዛ - ከአጠገባቸው እንደ ቆሙ -- ስነግርህ !! አዎን ዛሬ መለኮሻውን እየያዘ መዞር ጀምሯል። ግ.ሊ.ት ነገ ደግሞ የተለኮሰውን ሲጋራ በከንፈሩ እንደ ጨበጠ

ጢሱን እየማገልንና እየተፋልን ሲ.መ.ጣ ከመያዙ በፊት ከወዲሁ መታረም

አ.ለ.በ.ት ብዬ ነው፡፡

ዘሪሁን - ከተቀመጡበት አረፍ ብለው እየተነሱ - - ይሁንና ታዲያ ምን አለ --

ወደ በሩ ዞረው ይሄዳሉ

/መሸጋገሪያ ሙዚቃ /

/ ሁለቱም ተከታትለው እየሄዱ ይገቡና በሩን ዘግተው ይሰወራሉ /

# ትዕይንት አራት

4. ከላይኛው ቤት ሳሎን ውስጥ

ሮቤል እና እሌኒ ከወላጆቻቸው ፊት ለፊት ተቀምጠዋል

ሮቤል - ኮስተር ብሎ እማዬ ይሄን ያህል ለምን ታካብጂለሽ?

ዘሪሁን - ቆጣ ብሎ - - ሮቤል! በመጀመሪያ ይሄ ከየመንገዱ ላይ እና ከዚህ ከየቪዲዮው

የምትለቃቅማቸውን ቋንቋዎችህን ተዋቸውና ከእኛ ከወላጆችህ ጋር የምትነጋገር

ስለ መሆንህ አስተውለውና በአማርኛ እንነጋገር፡፡

ሮቤል - ፀጉሩን በጣቶቹ እየቆፈረ -- ኧ-ረ-አ-ባ- እ-ኔ እ-ኔ እኮ

ሮዛ - አቋርጣው ከፊት ለፊታቸው ካለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን የሲጋራ መለኮሻ

እየጠቆመች እና ለምን ይሄንን ነገር ያዝከው ብለን መጠየቅ አልነበረብንም፡፡

ሮቤል - እ-ህ ቆይ ግን እላዩ ላይ ያለውን ባትሪ ይታያችኋል?

ዘሪሁን - ብናየውም ሮቤል ለባትሪው ባትሪ ብቻ አለመያዙን ልቦናው ያውቃል፡፡

ሮዛ - አዎን በዚያ ላይ በወቅቱ ያየሁትን ባለመናገሬ እራሴን እንደ ጥፋተኛ ልቁጠረውና

ከዚህ በፊትም ያንን ነጩን ሸሚዝህን በማጥብበት ሰዓት ከኪሱ ውስጥ የሲጋራ

ፍርፋሪዎችን እንዳገኘሁኝ እነግርሃለሁ፡፡

ዘሪሁን - በድንጋጤ ቁጣ ሮዛ ላይ እያፈጠጠ -ምን!?

ሮቤል - ደንግጦ በመቃወም ኧረ አባዬ ...

ዘሪሁን - አቋርጦት - ቆይ አንተ ወደ ሮዛ ዞሮ በትዝብት ልሳን - ምነው ሮዛ?

"ይህች ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም" እንደሚባለው ይሄን ልጅ በወቅቱ መገሰጽና ጉዳትና ጥቅሙን እያስረዱ ማስተማር ሲገባን እንዲሁ ከተውነው በኋላ ዛሬ መለኮሻውን አይደለም ትንባሆዋን እያቦነነስ ብናገኘው ጥፋተኛ ነው ብለን ልንወቅሰው!?

ሮዛ - የዚያን ጊዜ ባለመናገሬማ ይሄውና ጥፋተኛ ሰለ መሆኔ አምኜ ይቅርታ ጠየኩኝ።

ዘሪሁን - እሱ ጥሩ - ወደ ልጆቹ ዞሮ በፈገግታ መነጋገር ይጀምራሉ

/መሸጋገሪያ ሙዚቃ ይገባል /

የቤተ ሰቡ አባላት በገጻቸው ላይ የነበረውን ድንጋጤ አስወግደው በሞቀ ፈገግታ እየተያዩና እየተሳሳቁ ሲነጋገሩ እየታዩ በላያቸው ላይ " ይህች ባቄላ ያደረች እንደ ሆን አትቆረጠምም" የሚለው አባባል በአዕምሯቸው ተንጸባረቀ።